# ተስፋኞቹን እና እንቅፋቶቹን መለየት ቢቻል



በዘውገ ፋንታ

ከዶ/ር እሸናፊ ጎሳዬ ጋር ውይይት

ዶ/ር አሸናፊ ጽሑፋቸውን ሲጀምሩ፣ *"የአገራችንን ፖለቲካ በቅርብ የምትከታተሉ ሰሞኑን ለነጻነት የሚደረገውን ጉዞ ለማዳከም የተከፈተውን ዘመቻ እና የዘንድሮውን አገር አቀፍ የምርጫ ውጤት ተከትሎ ብዙ አዳዲስ የሚመስሉ ነገር ግን የጠበቅናቸው ክስተቶች እንዳስተዋላችሁ እገምታለሁ"* ካሉ በኋላ፣ አራት ጉዳዮችን አመልክተዋል።

1ኛው ጉዳይ ተቀባይነት አለው። 2ኛው ጉዳይ፣ አሳሳቢ ነው። በድያስፖራው ኢትዮጵያውያን ላይ የተለያየ የፖለቲካ ድክመትና ችግር ሲጀመር ጀምሮ ሲተረክ የቆዬ ስለሆነ፣ የዶ/ር አሸናፊ ትዝብት፣ አዲስ አይሆንም። ስለዚህ፣ ዶ/ር አሸናፊ ያቀረቡት አስተያየት የሚያወያይ ነው። 3ኛው ነጥብ፣ የፖለቲካ ድርጅቶች የወሰዱትን አማራጭ ሂደት የሚያበስር ነው። *"ወያኔን በሚገባው ቋንቋ ለማነጋገርና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ዝግጅታችንን ጨርሰን የነጻነት ጉዞ ፊሽካ ነፍተን ጀምረናልና ነጻነት ናፋቂዎች ሁሉ ተቀላቀሉን ሲሉ ማወጃቸው"* በማለት የጻፉት፣ መልዕክት ያዘለ አወያይ ጉዳይ ነው። 4ኛው ጉዳይ የጽሑፉ ዋናው አላማ መሆኑን ንባቡ ያመለክታል።

የዚህ ጸሐፊ አላማ፣ ባንድ በኩል፣ ዶ/ር አሸናፊ ውይይት እንዲካሄድ በጠየቁት ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የተነሱበትን ጉዳይ ራሳቸው የጨለማ ኢላማ ስላደረጉት በዚያ ላይ ለመወያየት ነው። ይህን ሀሳባቸውን የሚከተለው ንባብ ያስረዳል፡ *"በተራ ቁጥር አራት የጠቀስኩትን ኃይል ማንነትና ድብቅ አላማ እንዲሁም በቅርቡ የትጥቅ ትግሉን አስመልክቶ የከፈተውን የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ በተመለከተ ጥያቄዎች ሊኖራቸው ስለሚችል የታዘብኩትን ባካፍልና በዚህ ጉዳይ ላይ በግልጽ መወያየት ብንጀምር ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ያግዛል ብዬ ስላመንኩ ነው።"* ይባል እንጂ፣ የቀረው ጽሑፍ ይህን አያመለክትም።

ይህ ጸሐፊ እንደ ዶ/ር አሸናፊ የስያትል ኗሪ ስለሆነ፣ እሳቸው እንዳሉት ያደረጉትን አስተዋጾ አጥብቆ ያውቃል፣ ያደንቃቸዋልም። ዳሩ ግን፣ አሁን ይዘው የቀረቡት የፖለቲካ ጎራ ሀሳብ፣ "የማንም ፖለቲካ ድርጅት ደጋፊ አይደለሁም" ያሉትን እንዳለ ያፈርሰዋል። እንደውም፣ እጅግ አሳሳቢ የፖለቲካ ሚና የሚቃኙ መሆናቸውን ይኼው ጽሑፋቸው (ኋላ እስረዳለሁ) አሳምሮ ይገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንኳን የአምስት ዓመቶች፣ የሃያ አምስትና አርባ አመቶችም ተሳትፎዎች አበላልጠውን አልተገኙም፣ ወይም የሚያበላልጡ አልሆኑም። ከዚህ ቀጥሎ፣ ዶ/ር አሸናፊ በአንቀጽ "ትዝብት አንድ እስከ ትዝብት አምስት፣ ከዚያም ላንባቢ ግምት ብለው ያቀረቡትን መልዕክቶችና የፖለቲካ አመለካከት እንደሚከተለው ለተጠየቀው ውይይት ይህ ጸሐፊ ያቀርባል።

**ትዝብት አንድ፥**

ዶ/ር አሸናፊ ሊገልጹ ያልፈለጉት ወይም ያልቻሉት ሰርጎ-ገብ ኃይል የተቃዋሚውን ሁሉ ኃይል የሚያፈርስ አካል እንዳለ በከረረና በመረረ ቃሎች ይገልጻሉ። *"አመራሩን እነሱ ካልተቆጣጠሩት የሚወስዱት እርምጃ ሁሌም አፍራሽና አደገኛ ነው"* ይሉና፣ *"መቼ ይሆን 'ዓላማችሁ ገብቶናል በቃችሁ' የምንላቸው?"* በማለት አንባቢን ወይም የፖለቲካ ጅርጅቶችን ይማለዳሉ። ዶ/ር አሸናፊ እሳቸው የሚያውቁትን አንባቢው እንዲገምት ከማድረግ ይልቅ፣ ፍግር ካለ፣ የብዕር ስም ተጠቅመው ይህን የፖለቲካ ድርጅት ሰርጎ-ገብ አካል ቢያጋልጡ ኖሮ ጥሩ መላ በተፈለገለት ነበር። የኢትዮጵያ ፖለቲካ የረጅም ዘመን ውጥንቅጥ አንዱ ምክንያት ይህ *'የጀርባ ጉሸሚያ* ነው።

**ትዝብት ሁለት፥**

ዶ/ር አሸናፊ ሰርጎ-ገብ ያስመሰሏቸውን የፖለቲካ ድርጅት ተከታዮች ቀልበስ ብለው የሚያደርጉትን መስዋዕትነት ይገልጻሉ። *"የነዚህን አፍራሽ ኃይሎች ድርጊት ያስተዋሉ ወገኖች፣ ወያኔ ወደ ተቃዋሚ ድርጅቶች አስርጎ ያስገባቸው ናቸው ብለው ይጠራጠራሉ። ጥርጣሬአቸው እውነት ቢመስልም ሀቁ ግን ሌላ ነው። እንዲያውም ወያኔንና የትግራይን ህዝብ መለየት እስከሚያቅታቸው ድረስ የወያኔን አምባገነንነት፣ ዘረኝነትና አድሎአዊ አገዛዝ ለማጋለጥ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ወያኔን ለመቃወም በተጠሩ ዝግጅቶች ሁሉ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሲሆኑ ገንዘባቸውንና ጊዜአቸውን ለመሰዋትም ወደኋላ አይሉም።"*

**ትዝብት ሶስት፥**

ዶ/ር አሸናፊ ሙገሳቸውን ይቀጥሉና፣ *"እነዚህ ኃይሎች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነትና ሉአላዊነት መቆማቸው ምንም ጥርጥር የለውም"* ካሉ በኋላ፣ ቀጥለው የራሳቸውን የፖለቲካ ዕምነት ግልጽ ያደርጋሉ፡ *"የብሄር ጥያቄ የሚያነሱና በዚያ መሰረት የተደራጁ ወገኖች ጋር ተቀራርቦ መስራት እንዳይቻል ዋነኛ እንቅፋት ሆነው መቆየታቸው ነው። በነሱ እምነት በአገራችን የመደብ እንጂ የብሄር ጭቆና መቼም ኖሮ አያውቅም።"* ዶ/ር አሸናፊ እኒህን ሰርጎ-ገቦች፣ መስዋዕት ከፋዮች፣ ሀገር ወዳዶች፣ የወያኔ ከባድ ጠንቆጭ፣ እንዲሁም ከፋፋዮች ምን እና ማን እንደሆኑ እስካልገለጹ ድረስ ጥሩ ጥርጣሬ ቢኖርም በግምት መጠቆሙ የፖለቲካ ኃጢአት ይሆናል። ግን ዶ/ር አሸናፊ ስለመሰከሩላቸው ስለ አንድ-ኢትዮጵያና አንድ-ሕዝብ ትግል አራማጅነታቸው፣ '**አምላክ ይባርካቸው**!' የሚባሉ ናቸው።

**ትዝብት አራት፥**

ዶ/ር አሸናፊ መካብና መናድን ስለደጋገሙ፣ ሀሳብዎ ተፋልሶ ይታያል፥ *"ወያኔን የሚጥለው ኃይል ከኬንያ፣ ከሱዳን፣ ከሱማሌ ወይም ከኤርትራ ቢነሳ ጉዳያቸው አይደለም። ዋንው ቁም ነገር ወያኔ ወድቆ ያ በሚስጥር የያዙት ዓላማቸው መሳካቱ ብቻ ነው። ታዲያ ሰሞኑን ከኤርትራ ተነስተን ተከዜን አቋርጠን አገራችንና ህዝባችንን ከወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ነጻ የማውጣት ጉዞአችንን ጀምረናል በሚሉት ኃይሎችና በህዝብ ተሳትፎ የቆመውንና አማራጭ የመረጃ ምንጭ የሆነው ሚዲያ ላይ ኃይለኛ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ የከፈቱት ለምንድነው?"* ፖለቲካ እንደ ሙቀጫ የገባለትን ሁሉ አብሮ ይፈጫል። ዶ/ር አሸናፊ በዚህ ላይ ይደገፋሉ። ትልቁ የፖለቲካ ሂደት ዕንቅፋት ከዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ ነው። አንድ ዓይናሞች በዛን!

**ትዝብት አምስት፥**

ዶ/ር አሸናፊ አስፈሪ ዕልቂት ሀሳብ ያቀርባሉ፤ *"የነዚህን ኃይሎች ፍጻሜ "ይህ የነጻነት ኃይል ከተሳካለት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የቆሙለትን አላማ ገድሎ እንደሚቀብረው ስለሚያውቁ ነው። የነጻነቱ ኃይል በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ አንዳርጋቸው ጽጌ ራዕይ የታነጸ፣ ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ ወጣቶች የተሰባሰቡበት እና ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩባት፣ የህግ የበላይነት የተረጋገጠባት፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተች ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረት እንደሚፈልግም ጠንቅቀው ይረዳሉ።"* በዚህ የዕልቂት ሀሳብዎ ምክንያት የሚደግፉት ድርጅት የሚደገፍ አይመስልም።

**ለአንባቢያ የተማለዱት፥**

ዶ/ር አሸናፊ የልባቸውን ቢናገሩም፣ እሳቸው የደበቁትን ሌላው እንዲገምት ይፈልጋሉ። እንዲህ ብለው ይገልጿቸዋል። *"የመጀመሪያዎቹ ብዙ ተከታይ ያላቸው ሲሆኑ ዋና ዓላማቸው ያለውን የአንድ ብሄር የበላይነትን አስወግዶ በሌላ መተካት ነው።"* ሌላውን ደግሞ በተንኮሉ አመሳስለው ያጣምሩታል። *"ሁለተኞቹ ደግሞ ዓለም የምትሽከረከረው በእነሱ ዙሪያ ብቻ የሚመስላቸው ግለሰቦች ሲሆኑ እነሱ ያልመሩት ድርጅት ወይም ትግል ውጤታማ ሲሆን ማየት ሞታቸው ስለሆነ ያንን ለማጨናገፍ የማይገቡበት የለም። እነዚህ ኃይሎች ናቸው እንግዲህ ግንባር ፈጥረው የነጻነት ጉዞውን ለማደናቀፍ ሌት ከቀን የሚሰሩት።"* ይህ አባባል 'ፈጣሪ' አለው፣ ተደገመ።

ድ/ር አሸናፊ ለመሆኑ ማንንና እነማንን ነው *"እነዚህ አፍራሽ ኃይሎች ያጠለቋቸውን ጭንብሎች እስወልቀን ካላጋለጥናቸው"* የሚሉት? ወይም "እኛ" የሚሏቸው? በተጨማሪም፣ ማንና ምንድን ነው 'ቁራሽ ቁራሹን' ይዞ የሚበታተነው? ዶ/ር አሸናፊ፣ ይመለሱና በግልጽ ይጻፉ፣ ድብቅብቆሹን ትተን በግልጽ ለመወያየት የሚሹ ከሆነ።